የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የህግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/ዳ/ 4347/18

ቀን፡- 23/11/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በቁጥር ኢንዱ/ኢንቨ/ቢ/373/18 በቀን 01/11/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የግብርና፣ሆርቲካልቸር እና አገልግሎት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መመሪያ በማዘጋጀት ህጋዊነቱ ተመርምሮ ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 147/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲውል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 31 ገጽ በዚህ ሽኜ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ዮናታን ጠብቀው ተሻለ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕ ቢሮ

Tel.No 058 222 0794/793 ✉ 995 Fax- 0582221530
☎ 058 220 37 57

የግብርና፣ሆርቲካልቸር እና አገልግሎት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መመሪያ

ቁጥር 147/2018 ዓ.ም

በተለያየ የአፈፃፀም ደረጃ ላይ የሚገኙትን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የልማት አፈፃፀም በመከታተል፤ ፕሮጀክቶች በተቆረጠ የማስጀመሪያ እና የማጠናቀቂያ ጊዜ፣በታቀደ የፕሮጀክት አፈፃፀም ለውጥ ወይም ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት በሚያስችል ሁኔታ ለመገምገምና ውጤት ለመሙላት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ውጤታማ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወደ ተለያዩ የአፈፃፀም ደረጃ በማስገባት የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅማቸውን በማሳደግ በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማት ላይ የላቀ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል በማስፈለጉ፤

በተለያየ ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሃብቶች ወይም ድርጅቶች ባቀረቡት የአዋጭነት ጥናት ሰነድና በገቡት ውል መሰረት ወደ ስራ መግባታቸውን በማረጋገጥ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን እውቅና ለመስጠት፤ያጋጠሙ ማነቆዎች ለመፍታት እና የአፈፃፀም ጉድለት ያለባቸውን በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የአስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 300/2017 አንቀፅ 25 እና አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 1 ፊደል ተራ (ሰ) ሥር ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የግብርና፣ ሆርቲካልቸርና አገልግሎት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መመሪያ ቁጥር 147/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ማለት ነው፤

2/ "መምሪያ" ማለት በዞን ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ የተቋቋመ ኢንዱስትሪናኢንቨስትመንት መምሪያ ነው፤

3/ "ጽህፈት ቤት" ማለት በወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ደረጃ የተቋቋመ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ነው፤

4/ "ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅትን ለማቋቋም፣ ወይም ነባር ድርጅትን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ለመግዛት፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤

5/ "የግብርና ኢንቨስትመንት" ማለት እንደ እንሰሳት እርባታ እና ማድለብ፣ በወተት ልማት፣ ዶሮና አዕዋፍ እርባታ፣ እንጉዳይ ምርት፤ ሐር ትል ልማት፣ በንብ ማነብ፣ በዓሳ ሀብት ልማት፣ የዱር እንስሳት እርባታ፣በጥምር ግብርና፣ ፣እፅዋትና የዕፅዋት ዘር ማልማት፣ሰብል ልማት፣ምርጥ ዘር ብዜት፣ሽንኩራ አገዳ እና ደን ልማት የመሳሰሉትን ዘርፎች የሚያጠቃልል ነው፤

6/ "ሆርቲካልቸር" ማለት እንደ አበባ፣አትክልት፣ፍራፍሬ፣ቡና፣ዕፀ-ጣዕም ማልማት እና የአትክትና ፍራፍሬ ዘር ብዜት በመሳሰሉት የኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚያጠቃልል ነው፤

7/ "አገልግሎት ኢንቨስትመንት" ማለት እንደ ባለ ኮከብ ሆቴል፣ ሞቴል፣ ሎጅ፣ ሪዞርት፣ የስፖርት ማዘውተሪያና ጅምናዚየም፣የአይሲቲና የፈጠራ ስራዎች፣ የትምህርት፣የጤና፣ የነዳጅ ዲፖ፣ማደያ፣የኤሌክትሪክ መኪና ቻርጅ፣ሪል ስቴት፣ አፓርታማ፣ የገበያ ማዕከል፣ ሞል፣ ሎጀስቲክ ወይም ዘመናዊ መጋዝን፣ ኢንቨስትመንት ዘርፎችን የሚያጠቃልል ነው፤

8/ “ባለሃብት” ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው፤

9/ “ድርጅት” ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

10/ “ኢንተርፕራይዝ” ማለት በንግድ ህጉ የተመዘገበ እና ህጋዊ ፈቃድ ያለው ሰዎች በጋራ ሆነው በግብርና፣በሆርቲካልቸር ወይም በአገልግሎት ዘርፍ ተሰማርተው ያለሙ የነበሩ እና የደረጃ ሽግግር ያደረጉ ማለት ነው፤

11/ “ሪል እስቴት” ማለት ለንግድ፣ ለመኖሪያ፤ ለኢንደስትሪ፤ ለማህበራዊ እና ለሌሎች አገልግሎት በመሬት ላይ እና ከመሬት በታች የተገነባ ግንባታ እና በመሬት ላይ የሚገኙ ቋሚ ተክሎችን የሚያካትት ነው፤

12/ “ሪል እስቴት ልማት” ማለት በመሬት ላይ እና ከመሬት በታች ለንግድ፤ ለመኖሪያነት፤ ለኢንደስትሪ፤ለማህበራዊ እና ለሌሎች አገልግሎት ለሽያጭ፣ ለኪራይ ወይም ሊዝ አገልግሎት እንዲውል ግንባታዎችን መገንባት ነው፤

13/ “የሪል እስቴት አልሚ” ማለት በአንድ ቦታ ወደ ጎን ወይም ወደ ላይ ከ1500 ካሬ ሜትር ጥቅል የግንባታ ወለል ስፋት በላይ የሆነ ቤት ወይም ቤቶች በግሉ ወይም ከመንግስት ወይንም ከሌሎች አካላትጋር በአጋርነት የሚገነባና በሽያጭ፤በሊዝ ወይንም በኪራይ ለተጠቃሚ የሚያቀርብ የተፈጥሮ ሰው/ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ማለት ነው፡፡

14/ “አውትግሮዎር” ማለት የግል ባለሀብቶች ተጨማሪ የግብርና ግብዓት /ምርት ፍላጎት ቢኖራቸው ይህንኑ በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ ተዋውለው የሚያስመርቱበት እና ውጤቱን የሚረከቡበት የአሰራር ስርዓት ማለት ነው፤

15/ “የኮንትራት እርሻ” ማለት ለተሻለ ምርትና ምርታማነት ባለሀብቶች ከመሬት ባለይዞታዎች ጋር በውል ስምምነት ላይ ተመሥርቶ በጋራ የመሥራት ዘዴ ነው፡፡

16/ “ውል ማደስ” ማለት ለኢንቨስትመንት በተለየ መሬት ላይ በሕግ መሠረት ቀድሞ በተገደበ ጊዜ የተያዘ ውልን ዘመኑ ሲጠናቀቅ እና በሌሎች ሕጋዊ ምክንያቶች በድጋሜ የሚሰጥ ውል ነው፤ ሆኖም በተለያዩ ሕጋዊ ምክንያቶች ውል ይዞ ከነበረ ባለ ሀብት ቀሪው ውል ዘመን ብቻ ወደ ሌላ ሕጋዊ አካል የሚደረግን የውል ምዝገባ አያካትትም፤

17/ “ማሽነሪ” ማለት እንደየ ፕሮጀክት ዓይነቱ የኢንቨስትመንት ተግባራትን ለማከናወን የሚያገለግል ዘመናዊ መሣሪያ ነው፤

18/ "አዋጭነትጥናት ሰነድ" ማለት የሰው ኃይል፣ በጀት ተመድቦለት እና በተወሰነ ጊዜ በግል ወይም በመንግሥት የሚከናወን ሲሆን ከቅድመ ግንባታ እስከ ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ያለዉን ጊዜ የሚያካትት ነዉ፤

19/ "ዓመታዊ የልማት አፈጻጸም ግምገማ" ማለት በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት መሬት የተሰጠው ሰው ባቀረበው አዋጭነት ጥናት ሰነድ መሠረት ፕሮጀክቱን ስለመተግበሩ እና ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

20/ "የልማት አፈፃፀም ገምጋሚ ቴክኒክ ኮሚቴ" በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎ የተሰማራ ባለሃብትን የልማት አፈፃፀም የሚገመግም የባለሙያዎች ቡድን ወይም ስብስብ ነው፤

21/ "አነስተኛ የግንባታ ደረጃ" ማለት የግንባታ ደረጃው G+0፣ G+1 እና G+2 የሆነ ለኢንቨስትመንት የሚውል ህንፃ ነው፤

22/ "መካከለኛ የግንባታ ደረጃ" ማለት የግንባታ ደረጃው G+3 የሆነ ለኢንቨስትመንት የሚውል ህንፃ ነው፤

23/ "ከፍተኛ የግንባታ ደረጃ" ማለት የግንባታ ደረጃው G+4 እና በላይ የሆነ ለኢንቨስትመንት የሚውል ህንፃ ነው።

24/ "ግንባታ መጀመር" ማለት በቦታው ላይ ለመሥራት ከተፈቀደው ግንባታ ወይም ሕንፃ፣ ቢያንስ የመሠረት ሥራ መሥራትና የኮለን ግንባታ ለማከናወን የሚያስችለ የኮለን ብረቶች የማቆም ሥራ ማጠናቀቅ ነው፤

25/ "ግንባታ ማጠናቀቅ" ማለት በሊዝ የተፈቀደ ቦታ ላይ እንዲገነባ የተፈቀደን ግንባታ በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ከሚመለከተዉ አካል የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲያገኝና ለአገልግሎት ዝግጁ ሲሆን ነው፤

26/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ፆታ ይጨምራል፤

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በግብርና፣ ሆርቲካልቸርና አገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፎች በተሰማራ ባለሀብት ወይም ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የልማት አፈፃፀም ግምገማ ውጤት አሰላል፣ መገምገሚያ መስፈርት እና ቅድመ ሁኔታዎች

4. መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ማንኛውም ባለሀብት ወይም ድርጅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦

1/ በበጀት ዓመቱ የታደሰ ፈቃድ ፤

2/ ምርት ወይም አገልግሎት መስጠት የጀመረ ከሆነ ንግድ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል

3/ ኢንቨስት እንዲያደርግ የተፈቀደበት የአዋጭነት ጥናት ሰነድ፤

4/ ፕሮጀክቱ ያለበትን ወቅታዊ የአፈፃፀም ደረጃ የሚገልፅ ሪፖርት እና ማስረጃ፤

5/ ከቀረጥ ነፃ የገቡ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች እና መሬት ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ፤

6/ በማህበራዊ አገልግሎት እና በመሠረተ ልማት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ስለማድረጉ ማረጋገጫ ማቅረብ ፤

7/ ቋሚና ጊዜአዊ ሥራ እድል መፍጠሩን የሚያሳይ የሠራተኛ ደመወዝ፣ የሥራ ግብር ክፍያ ተቀናሽ የሆነበት ፔሮል ማቅረብ፤

8/ ባለሃብቱ የተሻሻሉ የግብርና እና ሆርቲካልቸር ቴክኖሎጂዎችና ግብአቶችን ስለመጠቀሙና ተሞክሮውን ለአካባቢው አርሶ-አደሮች ስለማጋራቱ የሚያሳይ መረጃ በማዘጋጀት ማቅረብ አለበት።

5. መገምገሚያ መስፈርት አሰላል

እንደየ ፕሮጀክቱ ባህሪ መስፈርቶች ተካተው ውጤት የሚሞላ ቢሆንም፤ የሁሉም ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ የጋራ መስፈርቶች ከ60 ነጥብ የሚወሰድ ይሆናል፤

1/ ለተቋማዊ አደረጃጀት 10 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) ጽሕፈት ቤት ያለው 2 ነጥብ፤

ለ) የሰው ኃይል ቅጥር ለመፈፀም ባቀረበው የአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሠረት ቋሚ እና ጊዜያዊ ሰራተኛ 100% ቅጥር የፈፀመ 8 ነጥብ፤

ሐ) ቋሚ እና ጊዜያዊ የሠራተኛ ቅጥር ከ100% በታች የቀጠረ ከሆነ በፊደል ተራ "ለ" ላይ የተሰጠውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በተመጣጣኝ ስሌት (proportion) የሚሰራ ይሆናል።

2/ ካፒታል አጠቃቀም 20 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ በአዋጭነት ጥናት ሰነድ ባስቀመጠው መሰረት፡

ሀ) ካፒታሉን 100% መጠቀም የቻለ ከሆነ 20 ነጥብ፤

ለ) ከ100% በታች ስራ ላይ ካዋለ የፊደል ተራ"ሀ"መነሻ በማድረግ በተመጣጣኝ ስሌት (proportion) የሚሠራ ይሆናል።

3/ ምቹ የሆነ የሰራተኛ አያያዝ 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ በአዋጭነት ጥናት ሰነዱ መሠረት፡-

ሀ) የሠራተኞች አያያዝ ሙሉ በሙሉ የተሟላ ከሆነ 5 ነጥብ፤

ለ) የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት (first aid) እና መፀዳጃ ቤት ካሟላ 1 ነጥብ፤

ሐ) ለሥራ አስፈላጊ የሆነ አልባሳት እና ትራንስፖርት አገልግሎት ካሟላ 2 ነጥብ፤

መ) የሠራተኛ ደመወዝ በወቅቱ እየተከፈለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ ካሟላ 2 ነጥብ፤

ሠ) ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "መ" ከተቀመጡት አንዱንም ካላሟላ ነጥብ አይሰጥም።

4/ ወደ ልማት የገባ የመሬት መጠን 20 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ በአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሰረት

ሀ) በውል የተረከበውን መሬት 100% ለታለመለት ዓላማ ካዋለ 20 ነጥብ፤

ለ) በውል የተረከበውን መሬት ከ100% በታች ያለማ ከሆነ በፊደል ተራ "ሀ" ላይ የተሰጠውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በተመጣጣኝ ስሌት (proportion) የሚሰራ ይሆናል፤

5/ ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና አካባቢ ጥበቃ ስራዎች 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ በአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሰረት፡-

ሀ) በተራቆተው መሬቱ ላይ የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን እና ለአረንጓዴ ልማት ስራ ድጋፍ ያደረገ 5 ነጥብ፤

ለ) ለአረንጓዴ ልማት ስራ የአይነት ድጋፍ ብቻ ያደረገ 2 ነጥብ፤

ሐ) ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም።

6. <u>ሰብል ልማት እና ዘር ብዜት</u>

ለሰብል ልማት እና ዘር ብዜት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች ከ40 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል::

1/ የተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓት መጠቀም 20 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ በአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሠረት

ሀ) ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን የተጠቀመ ከሆነ 20 ነጥብ ፤

ለ) ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጅዎች ወይም ግብዓቶችን የተጠቀመ ከሆነ 10 ነጥብ ይሰጠዋል፤

ሐ) ምንም ዓይነት የግብርና ቴክኖሎጅም ሆነ ግብዓት ካልተጠቀመ ነጥብ አይሰጠውም።

2/ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ያበረከተው አስተዋጽኦ 10 ነጥብ ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ በአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሠረት፡-

ሀ) የአካባቢውን አርሶ አደሮች ተሞክሮዎችን ያካፈለ፣በአውትግሮዎር ወይም ኮንትራት ፋርሚንግ ውል ወስዶ ተጠቃሚ በማድረግ የገብያ ትስስር የፈጠረ፣ ለማህበራዊ አገልግሎት እና መሰረተ ልማት ግንባታ አስተዋኦ ያደረገ 10 ነጥብ፤

ለ) የአካባቢውን አርሶ አደሮች ተሞክሮዎችን በማካፈል፤ አውትግሮዎር ወይም ኮንትራት ፋርሚንግ ተጠቃሚ በማድረግ የገብያ ትስስር የፈጠሩ 7 ነጥብ፤

ሐ) ለአካባቢው ማህበረሰብ በማህበራዊ አገልግሎትና መሰረተ ልማት ግንባታ ድጋፍ አስተዋኦ ያደረገ 5 ነጥብ፤

መ) ለአካባቢው ማህበረሰብ ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ ካላደረግ ነጥብ አይሰጠውም።

3/ በአዋጭነት ጥናት ሰነዱ መሰረት ምርታቸውን ለገበያ ማቅረብ 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ እና እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያለው 5 ነጥብ፤

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ ወይም እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያለው 3 ነጥብ፤

ሐ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ገብያ ብቻ ያቀረበ 1 ነጥብ።

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ካለ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት ዓላማ ያዋለ 5 ነጥብ ይሰጠዋል፡

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ካለ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት ዓላማ ካላዋለ ነጥብ አይሰጠውም።

7. <u>የአትክልት፣ፍራፍሬ፣ቡና እና ዕፀ ጣዕም ልማት</u>

የአትክልት፣ፍራፍሬ፣ቡና እና ዕፀ ጣዕም ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ የተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓት መጠቀም 13 ነጥብ፤

ሀ) በምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የተለያዩ አትክልት፣ፍራፍሬ፣ቡና እና ዕፀ-ጣዕም ዝርያዎችን በዘመናዊ የማልሚያ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን በምክረ ሃሳብ መሰረት 100% የተጠቀመ ከሆነ 13 ነጥብ፤

ለ) በምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የተለያዩ አትክልት፣ፍራፍሬ፣ቡና እና ዕፀ-ጣዕም ዝርያዎችን በዘመናዊ የማልሚያ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን 75% እና በላይ የተጠቀመ ከሆነ 10 ነጥብ፤

ሐ) በምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የተለያዩ አትክልት፣ፍራፍሬ፣ቡና እና ዕፀ-ጣዕም ዝርያዎችን በዘመናዊ የማልሚያ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን 50 እስከ 74.9%የተጠቀመ ከሆነ 6 ነጥብ፤

መ) ከ50%በታች የተጠቀመ ከሆነ ነጥብ አይሰጠውም፤

2/ በአዋጭነት ጥናት ሰነዱ መሰረት ለአካባቢው ማህበረሰብ ያበረከተው አስተዋጽኦ (7 ነጥብ) ፦

ሀ) ውጤታማ የሆነ የአትክልትና ፍራፍሬ ዝርያዎችን በመጠቀም ሞዴል በመሆንና ተሞክሮውን ለአካባቢው ማህበረሰብ ያካፈለ፣አርሶ አደሮችን በአውት ግሮዎር እና ኮንትራት ፋርሚንግ የአሰራር ዘዴ በማደራጀት ተጠቃሚ ያደረገ 7 ነጥብ ይሰጠዋል፤

ለ) የአካባቢውን አርሶ አደሮች በአውት ግሮዎር እና ኮንትራት ፋርሚንግ የአሰራር ዘዴ ብቻ በማደራጀት ተጠቃሚ ያደረገ 5 ነጥብ ይሰጠዋል፤

ሐ) ለአካባቢው ማህበረሰብ በማህበራዊ አገልግሎትና መሰረተ ልማት አስተዋፅኦ ያደረገ 3 ነጥብ፤

መ) ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሐ" ከተዘረዘሩት አንድም አስተዋፅኦ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም፡፡

3/ በአዋጭነት ጥናት ሰነዱ መሠረት ምርቱን ለገበያ ያቀረበ 15 ነጥብ የሚይዝ ሲሆን፦

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ እና እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረበ 15 ነጥብ፤

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ ያቀረበ ወይም እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ መሆኑን በሰነድ ያረጋገጠ 7 ነጥብ፤

ሐ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ለገብያ ያቀረበ 3 ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም (5 ነጥብ) የሚይዝ ሲሆን፡-

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ካለ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት ዓላማ ያዋለ 5 ነጥብ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ካለ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት ዓላማ ካላዋለ ነጥብ አይሰጠውም፡፡

8. ለአበባ ልማት

ለአበባ ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል-

1/ በአዋጭነት ጥናት ሰነዱ መሰረት ቴክኖሎጂ እና ግብዓት መጠቀም 10 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ፦

ሀ) ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችንና ግብዓቶችን ተጠቅሞ በማምረት ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች እና ሙያተኞች የእውቀት ሽግግር ያደረገ 10 ነጥብ ይሰጠዋል፤

ለ) ዘመናዊ ቴክኖሎጅ እና ግብዓቶች ተጠቅሞ ያለማ ወይም ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች እና ሙያተኞች የእውቀት ሽግግር ያደረገ 5 ነጥብ ይሰጠዋል፤

ሐ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" ሳይጠቀም የሚያለማ ከሆነ ነጥብ አይሰጠውም፡

2/ ለአካባቢው ማህበረሰብ ያበረከተው አስተዋጽኦ 5 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ፦

ሀ) ለአካባቢው ማህበረሰብ በመሰረተ ልማት እና በማህበራዊ አገልግሎት አስተዋፅኦ ያደረገ 5 ነጥብ፤

ለ) ለአካባቢው ማህበረሰብ ለመሰረተ ልማት ግንባታ ወይም ማህበራዊ አገልግሎት አስተዋፅኦ ያደረገ 2 ነጥብ፤

3/ ምርቱን ለውጭ ገብያ ማቅረብ 20 ነጥብ የሚያሰጥ ሲሆን፦

ሀ) የምርቱን 75% እና በላይ የሚሆነውን ለውጭ ያቀረበ 20 ነጥብ ፤

ለ) የምርቱን ከ75% በታች ለውጭ ገበያ ያቀረበ ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በተመጣጣኝ ስሌት (proportion) የሚሰራ ይሆናል።

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 5 ነጥብ የሚያሰጥ ሲሆን

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያዋለ 5 ነጥብ ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ካላዋለ ነጥብ አይሰጠውም።

9. የእንስሳት እርባታ እና ማድለብ

የእንስሳት እርባታ እና ማድለብ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን እና ግብዓቶችን መጠቀም 17 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ፦

ሀ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የእንስሳት ዝርያዎች የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ተጠቅሞ ማርባት እና ማድለብ 17 ነጥብ፤

ለ) ዘርፉን ውጤታማ ለማድርግ የሚያስችል የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች ወይም ግብዓቶችን የተጠቀመ 10 ነጥብ፤

ሐ) የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች፣ቴክኖሎጂ እና ግብዓት ያለመጠቀም ውጤት አይሰጠውም

2/ ለአካባቢው ማህበረሰብ ያደረገው አስተዋጽኦ 10 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ

ሀ) የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን፣ቴክኖሎጅዎች እና ግብአቶች በመጠቀም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሞዴል የሆነ እና ልምዱን ያካፈለ ከሆነ 10 ነጥብ፤

ለ) የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን ወይም ቴክኖሎጅዎች እና ግብአቶች በመጠቀም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሞዴል የሆነ እና ልምዱን ያካፈለ ከሆነ 5 ነጥብ፤

ሐ) የአካባቢውን ማህበረሰብ በመሰረተ ልማትና በማህበራዊ አገልግሎት አስተዋፅኦ ያደረገ 2 ነጥብ፤

3/ በአዋጭነት ጥናት ሰነዱ መሠረት ምርቱን ለገበያ ማቅረብ 8 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ እና እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረበ 8 ነጥብ፣

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ ወይም እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረበ 4 ነጥብ፣

ሐ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ገብያ ብቻ ያቀረበ 1 ነጥብ።

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያዋለ 5 ነጥብ ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያላዋለ ነጥብ አይሰጠውም።

10. <u>የደሮ ሃብት ልማት</u>

የደሮ ሃብት ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን እና ግብዓቶችን መጠቀም 16 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ

ሀ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የደሮ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን በምክረ ሃሳቡ መሰረት ሙሉ በሙሉ የተጠቀመ 16 ነጥብ፤

ለ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የደሮ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን 75% በላይ የተጠቀመ 10 ነጥብ፤

ሐ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የደሮ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ

ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ከ50 እስከ 75% የተጠቀመ 10 ነጥብ፤

መ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የደሮ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ከ50% በታች የተጠቀመ ነጥብ አይሰጥም፤

2/ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ያደረገው አስተዋጽኦ 10 ነጥብ የሚያሰጠው ሆኖ

ሀ) የተሻሻሉ የደሮ ዝርያዎችን በመጠቀም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሞዴል የሆነና ተሞክሮውን ያካፈለ ከሆነ ያቀረበ 10 ነጥብ፤

ለ) የተሻሻሉ የደሮ ዝርያዎችን በመጠቀም ያለማ ከሆነ 8 ነጥብ፤

ሐ) ለአካባቢው ማኅበረሰብ በመሰረተ ልማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት ልማት ድጋፍ ያደረገ 5 ነጥብ፤

መ) በፊደል ተራ ከ"ሀ" እስከ "ሐ" ከተሰረዘሩት አንዱንም ካላሟላ ነጥብ አይሰጠውም

3/ ምርቱን ለገብያ ያቀረበ 7 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ የሚልክ፣ እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ስለማቅረቡ በሰነድ ያረጋገጠ 7 ነጥብ፤

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ የሚልክ ወይም እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ስለማቅረቡ በሰነድ ያረጋገጠ 4 ነጥብ፤

ሐ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ገብያ ብቻ ያቀረበ 1 ነጥብ ይሰጠዋል፤

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 7 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያዋለ 7 ነጥብ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያላዋለ ነጥብ አይሰጠውም።

11.የአሳ ሃብት ልማት

የአሳ ኃብት ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን እና ግብዓቶችን መጠቀም 16 ነጥብ የሚያሰጥ

ሀ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የአሳ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን በምክረ ሃሳቡ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደረገ 16 ነጥብ፤

ለ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የአሳ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን 75% በላይ ተግባራዊ ያደረገ 10 ነጥብ፤

ሐ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የአሳ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ከ50 እስከ 75% ተግባራዊ ያደረገ 10 ነጥብ፤

መ) በጥናትና ምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የአሳ ዝርያዎች ለማርባት የተለያዩ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ከ50% በታች ተግባራዊ ያደረገ ነጥብ አይሰጥም፤

2/ ለአካባቢው ማህበረሰብ ያደረገው አስተዋጽኦ 10 ነጥብ የሚያሰጠው ሆኖ

ሀ) የተሻሻሉ የአሳ ዝርያዎችን በመጠቀም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሞዴል የሆነና ተሞክሮውን ያካፈለ ከሆነ 10 ነጥብ፤

ለ) የተሻሻሉ የአሳ ዝርያዎችን በመጠቀም ያለማ ነገር ግን ተሞክሮ ያላካፈለ ከሆነ 5 ነጥብ፤

ሐ) ለአካባቢው ማኅበረሰብ በመሰረተ ልማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት ልማት ድጋፍ ያደረገ 5 ነጥብ፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ"ሀ" ን "ለ" ን እና "ሐ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

3/ ምርቱን ለገብያ ያቀረበ 8 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ እና እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ስለማቅረቡ በሰነድ ያረጋገጠ ከሆነ 8 ነጥብ፤

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ ወይም እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ስለማቅረቡ በሰነድ ያረጋገጠ ከሆነ 4 ነጥብ፤

ሐ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ገብያ ብቻ ያቀረበ 1 ነጥብ ይሰጠዋል፤

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 6 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያዋለ 6 ነጥብ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያላዋለ ነጥብ አይሰጠውም፤

12. <u>የደን ልማት</u>

የደን ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ ዘመናዊ ቴክኖሎጅና ግብዓት መጠቀም 15 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ለደን ልማት አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂ እና ግብዓት ተጠቅሞ የተሻሻሉ ገብያ ተኮር የሀገር በቀል ችግኞችን በችግኝ ጣቢያዎ ማባዛት የቻለ 15 ነጥብ፤

ለ) ለደን ልማት አስፈላጊ የሆነ የችግኝ ጣቢያዎችን በማቋቋም የሀገር በቀል ችግኞችን በማባዛት የቻለ 7 ነጥብ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም።

2/ ለአካባቢው ማህበረሰብ የተደረገ አስተዋፅኦ 15 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) ገብያ ተኮር የሆኑ የደን ዓይነቶችን በመጠቀም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሞዴል በመሆንና ተሞክሮው በማካፈል ተጠቃሚ ያደረገ 15 ነጥብ፤

ለ) የተሻሻሉ የችግኝ ዝርያዎችን ለአካባቢው ማህበረሰብ ያቀረበ 7 ነጥብ፤

ሐ) ለአካባቢው ማኅበረሰብ በመሰረተ ልማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት ልማት አስተዋፅኦ ያድረገ 2 ነጥብ፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ"ሀ" ን፤ "ለ" ን እና "ሐ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም፤

3/ ምርቱን ለገብያ ያቀረበ 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ እና ለአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ያቀረበ 5 ነጥብ፣

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ ወይም ለአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ 3 ነጥብ፤

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያዋለ 5 ነጥብ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያላዋለ ነጥብ አይሰጠውም፤

13. ለንብ ማነብ

ለንብ ማነብ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እና ግብዓት መጠቀም 10 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ

ሀ) ዘመናዊ የንብ ማነብ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ተግባራዊ ያደረገ 10 ነጥብ፤

ለ) ዘመናዊ የንብ ማነብ ቴክኖሎጅዎች ወይም ግብዓቶችን ተግባራዊ ያደረገ 5 ነጥብ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

2/ ምቹ አካባቢ መፍጠር 10 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) የቀሰም ተክሎችን በመትከል ጥቅም ላይ በማዋል ምቹ የሆነ መጠለያ እና የውሃ አቅርቦትን ያሟላ 10 ነጥብ፤

ለ) ምቹ የሆነ መጠለያ እና የውሃ አቅርቦትን ያሟላ 5 ነጥብ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

3/ ለአካባቢው ማህበረሰብ ያደረገው አስተዋፅኦ 10 ነጥብ የሚይዝ ሲሆን

ሀ) ቴክኖሎጅና ግብዓት በመጠቀም ለአካባቢውን ማህበረሰብ ሞዴል የሆና እና ልምዱን ያካፈለ 10 ነጥብ፤

ለ) በዘርፉ ለአካባቢው ማህበረሰብ ስልጠና የሰጠ 2 ነጥብ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

4/ ምርቱን ለገብያ ያቀረበ 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ እና ምርቱን እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ መሆኑን በሰነድ ያቀረበ 5 ነጥብ፤

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ ወይም ምርቱን እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረበ 2 ነጥብ፤

ሐ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ገብያ ብቻ ያቀረበ 1 ነጥብ፤

5/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 5 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያዋለ 5 ነጥብ ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያላዋለ ከሆነ ነጥብ አይሰጠውም፤

14. ጥምር ግብርና

ለጥምር ግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ የተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓት መጠቀም 13 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ

ሀ) ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የተለያዩ የማልሚያ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ባቀረበው የአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሰረት ከ95% እና በላይ የተጠቀመ ከሆነ 13 ነጥብ፤

ለ) ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የተለያዩ የማልሚያ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ባቀረበው የአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሰረት ከ75 እስከ 94.9% የተጠቀመ ከሆነ 10 ነጥብ፤

ሐ) ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የተለያዩ የማልሚያ ቴክኖሎጅዎች እና ግብዓቶችን ባቀረበው የአዋጭነት ጥናት ሰነድ መሰረት ከ50 እስከ 74.9% የተጠቀመ ከሆነ 6 ነጥብ

መ) ከ50% በታች የተጠቀመ ከሆነ ነጥብ አይሰጠውም፤

2/ ለአካባቢው ማህበረሰብ ያበረከተው አስተዋጽኦ 7 ነጥብ የሚያሰጥ ሆኖ

ሀ) በዘርፉ ውጤታማ በመሆን ተሞክሮውን ለአካባቢው ማህበረሰብ ያካፈለ በማህበራዊ መሰረተ ልማት አስተዋፅኦ ያደረገ 7 ነጥብ፤

ለ) በዘርፉ ውጤታማ የሆነ ነገር ግን ለአካባቢው ማህበረሰብ ተሞክሮን ያላካፈለ ከሆነ 4 ነጥብ፤

ሐ) ለአካባቢው ማህበረሰብ በማህበራዊ አገልግሎትና መሰረተ ልማት አስተዋፅኦ ያደረገ 4 ነጥብ፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሐ" ከተዘረዘሩት አንድም አስተዋፅኦ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም።

3/ ምርቱን ለገበያ ያቀረበ 15 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) ምርቱን ለውጭ ገብያ እና እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረበ 15 ነጥብ፤

ለ) ምርቱን ለውጭ ገብያ ያቀረበ ወይም እሴት ለሚጨምሩ ለአገር ውስጥ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያቀረበ መሆኑን በሰነድ ያረጋገጠ 7 ነጥብ፤

ሐ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ለገብያ ያቀረበ 3 ነጥብ ይሰጠዋል።

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 5 ነጥብ የሚይዝ ሲሆን፦

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ካለ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት ዓላማ ያዋለ 5 ነጥብ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ካለ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት ዓላማ ካላዋለ ነጥብ አይሰጠውም።

15. <u>አገልግሎት ኢንቨስትመንት</u>

ለአገልግሎት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ የግንባታ ግብዓቶችን እና ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ማሽነሪዎችን ማሟላት 10 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ፤

ሀ) ለግንባታው አገልግሎት የሚውሉ ጥራታቸውን የጠበቁ የሀገር ውስጥ ግብዓቶችን እና የተለያዩ ማሽነሪዎችን የተጠቀመ 10 ነጥብ፤

ለ) በአገር ውስጥ የማይገኙ ጥራት ያላቸውን የግንባታ ግብዓቶችን ከውጭ በማስገባት እና የተለያዩ ማሽነሪዎችን የተጠቀመ 7 ነጥብ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

2/ የግንባታ ሂደት 10 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ግንባታውን በተቀመጠለት የድርጊት መርሃ ግብር እና ግንባታ ፈቃድ መሰረት ያስኬደ 10 ነጥብ፤

ለ) ግንባታውን በተቀመጠለት የድርጊት መርሃ ግብር እና ግንባታ ፈቃድ ውጭ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ግንባታውን ያጓተተ ከሆነ ነጥብ አይሰጠውም፤

3/ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ያደረገው አስተዋጽኦ 5 ነጥብ

ሀ) ለአካባቢው ማኅበረሰብ በመሰረተ ልማት ግንባታ እና ማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ ያደረገ ከሆነ 5 ነጥብ ይሰጣል፤

ለ) ለአካባቢው ማኅበረሰብ በመሰረተ ልማት ግንባታ ወይም ማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ ያደረገ ከሆነ 2 ነጥብ ይሰጣል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

4/ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ማበረታቻዎች አጠቃቀም 10 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ

ሀ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉበሙሉ ለታለመለት አላማ ያዋለ 10 ነጥብ ፤

ለ) ከቀረጥ ነፃ የገባን ማበረታቻ ሙሉ በሙሉ ለታለመለት አላማ ያላዋለ ነጥብ አያገኝም።

16. <u>ሪል እስቴት</u>

ለሪል እስቴት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርቶች 40 ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል

1/ የግንባታ ግብዓቶችን እና ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ማሽነሪዎችን ማሟላት 15 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ፤

ሀ) ለግንባታው አገልግሎት የሚውሉ የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ ወይም የውጭና አገር ውስጥ የግንባታ ግብዓት እና የግንባታውን ስራ ማቀላጠፍ የሚያስችል የተለያዩ ማሽነሪዎችን የተጠቀመ ከሆነ 15 ነጥብ፤

ለ) በሚመለከተው አካል የጥራት ደረጃ እውቅና ባገኘ የአገር ውስጥ ወይም ከውጭ በገባ ወይም በውጭና በአገር ውስጥ የግንባታ ግብዓት የተጠቀመ ነገር ግን ስራን ማቀላጠፍ የሚያስችል የግንባታ ማሽነሪ ካልተጠቀመ 10 ነጥብ፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

2/ የግንባታ ሂደት 15 ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን

ሀ) ግንባታውን በተቀመጠለት የድርጊት መርሃ ግብር እና የግንባታ ፈቃድ መሰረት ያስኬድ ከሆነ 15 ነጥብ፤

ለ) ግንባታውን በተቀመጠለት የድርጊት መርሃ ግብር እና ግንባታ ፈቃድ ውጭ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ግንባታውን ያጓተተ ከሆነ ነጥብ አይሰጠውም፤

3/ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በኢኮኖሚ ልማት፣በመሠረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ያደረገ 10 ነጥብ የሚይዝ ሲሆን፦

ሀ) በፕሮጀክቱ ምክንያት የልማት ተነሽዎችን በማደራጀት ለተለያዩ የንግድ ወይም የመኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ ያስረከበ ከሆነ 10 ነጥብ፤

ለ) ለአካባቢው ማኅበረ ሰብ ለተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት ወይም መሰረት ልማት ድጋፍ ያደረገ 5 ነጥብ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ"ን ተግባራዊ ካላደረገ ነጥብ አይሰጠውም

ክፍል ሶስት

ስለ ሪፖርት አቀራረብና ውጤቱ አገላለፅ ፣ እርምጃ አወሳሰድ እና ቅሬታ ስለማስተናገድ፡-

17. የፕሮጀክት የልማት አፈፃፀም ግምገማ የሪፖርት አቀራረብ እና የውጤቱ አገላለፅ

የፕሮጀክት የልማት አፈፃፀም ግምገማ የሪፖርት አቀራረብ እና የውጤቱ አገላለፅ በሚከተለው መልኩ ይከናወናል፡-

1/ የኢንቨስትመንት የልማት አፈፃፀም ገምጋሚ ቴክኒክ ኮሚቴ በመስክ የገመገመውን የፕሮጀክቶችን ልማት አፈፃፀም የሪፖርት ውጤት በ15 ቀናት ውስጥ በየደረጃው ለሚገኝ የኢንዱስትሪና እንቨስትመንት ተቋም ያቀርባል፤

2/ በየደረጃው የሚገኘው የኢንዱስትሪና እንቨስትመንት ተቋም ኃላፊ በቴክኒክ ኮሚቴ የቀረበውን የልማት አፈፃፀም ሪፖርት ውጤት በማኔጅመንት አባላት ካስገመገመ በኋላ የውጤቱን ውሳኔ በአስር የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ በደብዳቤ ወይም በማስታወቂያ ያሳውቃል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንተጠበቀ ሆኖ የጽ/ቤት ኃላፊው የቴክኒክ ኮሚቴውን ሪፖርት ውጤት በማኔጅመንት ካስገመገመ በኋላ በመሙያ ቅፁ የተሞላውን ከልማት አፈፃፀም ውጤት ጋር ለኢንቨስትመንት ቦርድ በማቅረብ የቦርዱን የውሳኔ አስተያየት ለመምሪያው ይልካል፤

4/ የመምሪያው ኃላፊ የቦርዱን የውሳኔ አስተያየት እና በልማት አፈፃፀም መሙያ ቅፁ የተሞላውን የሰብል የልማት አፈፃፀም ውጤት እስከ ህዳር 30 ፤ እንዲሁም የሌሎች ፕሮጀክቶች የልማት አፈፃፀም እስከ ሰኔ 15 ተሞልቶ ለቢሮው ይልካል፤

5/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመታዊ የልማት አፈፃፀም ውጤታቸው ከበጀት ዓመቱ የሚሻገር ከሆነ አንድ ዓመት በሚሞላበት ወር ውስጥ ውጤቱ የሚሞላ ይሆናል፤

6/ በመምርያ ደረጃ ያለ ኢንቨስትመንት ቦርድ እና በቢሮው የተሰጠን ውሳኔ ጽህፈት ቤቱ ውሳኔው በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

7 ለሁሉም ፕሮጀክቶች የመሬት ውል ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በየሩብ አመቱ ድጋፍና ክትትል በማድረግና መረጃዎች ይደራጃሉ፣በአመቱ መጨረሻ የፕሮጀክቱ የልማት አፈፃፀም ግምገማ ውጤቱ የሚሞላ ይሆናል፤

18. ለኢንቨስትመንት የተላለፈ መሬት ውል ስለማቋረጥና እርምጃ አወሳሰድ

በሚከተሉት ምክንያቶች ውል ሊቋረጥ ይችላል፡-

1/ በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታ ካልተጀመረ፣ ይራዘምልኝ ጥያቄ አቀርቦ ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ ወይም በተሰጠዉ ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ግንባታ ያልጀመረ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

2/ አግባብ ባለው አካል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም ንግድ ፈቃዱ ሲሰረዝ፣

3/ በራስ ፈቃድ መሬቱን የመልቀቅ ወይም ውል የማቋረጥ ጥያቄ በጽሑፍ ሲያቀርብ፤

4/ በዚህ መመሪያና በሌሎች ሕግጋት የተደነገጉ ግዴታዎች እንዲሁም ባቀረበው የአዋጭነት ጥናት ሰነድ እና በውሉ መሠረት ለሁለተኛ ተከታታይ ጊዜ የልማት አፈፃፀም ውጤቱ ከ50 በመቶ በታች ከሆነ ወይም መሬቱን ካላለማ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካለው ፈቃዱ እንዲሰረዝ ተደርጎ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ ይመለሳል፤

5/ ዓመታዊ የልማት አፈፃፀም ውጤት ከ50 በመቶ በላይ ሆኖ ከተረከበው መሬት ውስጥ መልማት ከሚችለው መሬት 60 በመቶ እና በላይ ማልማት ካልቻለ ሙሉ በሙሉ እንዳላለማ ተቆጥሮ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ይደረጋል።

6/ ባለሃብቶች በማኅበር ወይም በፒኤልሲ ተደራጅተው የኢንቨስትመንት መሬት ከወሰዱ በኋላ ማኅበሩ በሕግ የፈረሰ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ውሉ ተሰርዞ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ ሲገባ፤

7/ የውል ዘመኑ ባይጠናቀቅም ያለ በቂ ምክንያት የልማት አፈጻጸም ውጤቱ ከ50 በመቶ በታች

ከሆነ ወይም መሬቱን ጸም ያሳደረ ሆኖ ሲገኝ፤

8/ በተወሰነለት የመሬት መጠንና ውል መሰረት በቦታው ላይ በግንባታ ፈቃዱ መሰረት ያለበቂ ምክንያት ሥራ ሳይጀምር ሲቀር፤

9/ መሬቱን ለተሻለ የሕዝብ አገልግሎት መንግስት የፈለገው ከሆነ፤

10/ መሬቱን ለሦስተኛ ወገን ማከራየቱ በማስረጃ ሲረጋገጥ፤

11/ በተረከበው መሬት ላይ የተፈጥሮ ሀብትን አለግባብ በመጠቀም በአካባቢው ጉዳት ማድረሱ በሚመለከተው ተቋም ሲረጋገጥ እና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነዱ ሲሰረዝ፤

12/ በአበዳሪ ተቋማት ለሦስተኛ ወገን የተላለፈ መሬት የመጀመሪያው ተበዳሪ የኪራይ ውል ዘመን ሲጠናቀቅ።

13/ ስልጣን ባለው አካል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካለው መሰረዙ ሲረጋገጥ፤

14/ በሞት ሲለይ ወራሽ ከሌለው ውሉ ፈርሶ ወደ መሬቱ ባንክ ይገባል።

19. ቅሬታ ስለማስተናገድ፡-

በየደረጃው የሚገኝ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም በዚህ መመሪያ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቅሬታዎችን የሚስተናግድ ሆኖ፡-

1/ በፕሮጀክት አፈፃፀም ግምገማ ውጤት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያለው ውጤቱ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ አምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታቸውን በፅሁፍ ለሃላፊው ያቀርባሉ፤ ኃላፊው የቀረቡትን ቅሬታዎች በማኔጅመንት በማየት በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በፅሑፍ ምላሽ ይሰጣል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ውሳኔ ያልረካ ለኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢው ቅሬታውን በ ሰባት (7) የሥራ ቀናት ውስጥ በፅሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፣ በየደረጃው በመምሪያ ወይም በጽህፈት ቤት ደረጃ የሚገኘው ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰባሳቢ ቅሬታውን ተመልክቶ በ አስር (10) የስራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በፅሑፍ ምላሽ ይሰጣል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ውሳኔ ያልረካ ቅሬታው በጹህፍ ለቢሮው በ ሰባት (7) የስራ ቀናት ውስጥ በማቅረብ ቢሮው በ አስራአምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፤

4/ በቢሮው ቴክኒክ ኮሚቴ የታዩ ፕሮጀክት አፈፃፀም ግምገማ ውጤት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያለው ቅሬታቸውን በ ሰባት (7) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለቢሮው ያቀርባሉ፤ ቢሮው ቅሬታውን አይቶ በ አስራአምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ውሳኔውን በጽሁፍ ያሳውቃል፤

5/ በቢሮው ውሳኔ ያልረካ በ ሰባት (7) የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰባሳቢ ያቀርባል፤የክልሉ ቦርድ ሰባሳቢ ቅሬታውን አይቶ በ15 ቀን ውስጥ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አስከ 5 ከተደነገገው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎ የቀረበ ቅሬታ ተቀባይነት አያገኝም፤

ክፍል አራት

ስለ መመሪያው አስፈፃሚ አካላት፣ ውጤት አሰጣጥ ሥርዓት እና የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መዋቅር ተግባርና ኃላፊነት፣

20. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

1/ ልዩ ክልላዊ ፋይዳ ያላቸውን የግብርና፣ሆርቲካልቸር እና አገልግሎት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ከመምሪያዎች እና ጽህፈት ቤቶች ጋር በመቀናጀት ልማት አፈፃፀም ውጤት ሊሞላ ይችላል፤ የአፈፃፀም ችግር ያለባቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ደግፎ ወደ ስራ ያስገባል፤

2/ ከመምሪያዎች እና ጽህፈት ቤቶች የልማት አፈፃፀም ውጤት ህግና አሰራርን ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ ናሙና በመውሰድ የማረጋገጥ፣ድጋፍና ክትትል የማድረግ ስራ ያከናውናል

3/ ለኢንቨስትመንት የተላለፈ መሬት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ፣ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ ይሰራል፣ከታለመለት ዓላማ ውጭ ያዋሉትን ለአንድ ጊዜ የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤በማስጠንቀቂያው መሰረት ፈጥኖ ወደስራ የማይገባ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካለው ፈቃዱ ተሰርዞ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ እና ውል እንዲቋረጥ ለመሬት ተቋም በደብዳቤ ያሳውቃል፣ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

4/ ከመምሪያዎች የልማት አፈፃፀም ውጤት የተሞላላቸውን ፕሮጀክት ይረከባል፣አደራጅቶ ይይዛል፤

5/ ከቀረጥ ነፃ የገባው ሃብት በተገቢው መንገድ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ፣ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ ይሰራል፣ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ያላዋሉት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

6/ ከኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ከመሬት አስተዳድርና አጠቃቀም ዙርያ የሚነሱ ችግሮችን ከክልሉ መሬት ቢሮ ጋር በመቀናጀት ችግሩን ይፈታል፤

7/ የመጠቀም መብት በእዳ ዋስትና በተያዘ መሬት ላይ የባለሃብቱ ዓመታዊ የልማት አፈፃፀም ውጤት ከ50% በታች ሆኖ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ውጤቱን ለአበዳሪው ተቋም በቅጅ የማሳወቅ ስራ ይሰራል፤

8/ በክልል ደረጃ ከባለሃብቶች ቄም ድርጅቶች ጋር የምክክር መድርኮችን ያዘጋጃል፤

9/ በክልሉ የኢንቨስትመንት ቦርድ የሚሰጡ ውሳኔዎችን እና አቅጣጫዎችን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤ይከታተላል።

21. የመምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

1/ በጽህፈት ቤት በኩል የቀረቡ የልማት አፈፃፀም ውጤት መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ችግር ያለባቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ደግፎ ወደ ስራ ያስገባል፤

2/ በጽህፈት ቤት የልማት አፈፃፀም ውጤት አሰጣጥ እና እርምጃ አወሳሰድ ህግና አሰራርን ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ ናሙና በመውሰድ የማረጋገጥ፣ድጋፍና ክትትል የማድረግ ስራ ያከናውናል፤

3/ በመምሪያው ስር የሚገኙ ፕሮጅክቶችን የልማት አፈፃፀም ውጤት ይሞላል፤

4/ የልማት አፈፃፀም ውጤት መነሻ በማድረግ የቦርዱን የውሳኔ አስተያየት ለቢሮው ይልካል፤

5/ ለኢንቨስትመንት በተሰጠው መሬት ላይ በአግባቡ ማልማት ካልቻሉ ለአንድ ጊዜ የፁሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ማልማት ካልቻሉ መሬቱን ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ የውሳኔ አስተያይቱን ለቦርዱ በማቅረብ ያስወስናል፤ውሳኔውን ለቢሮው ያሳውቃል፤

6/ ከቀረጥ ነፃ የገባው ሃብት በተገቢው መንገድ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ፣ ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ ይሰራል፣ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ያላዋሉትን እርምጃ እንዲወሰድ ውሳኔ አስተያየት ለቢሮው ያቀርባል፤

8/ ከኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ከመሬት አስተዳድርና አጠቃቅም ዙርያ የሚነሱ ችግሮች ካሉ ከመሬት መምሪያ ጋር በመቀናጀት ችግሩን ለይቶ ይፈታል፤ ከአቅም በላይ ከሆነ ለቢሮው በሪፖርት ያሳውቃል፤

9/ የመጠቀም መብት በእዳ ዋስትና በተያዘ መሬት ላይ የባለሃብቱ ዓመታዊ የልማት አፈፃፀም ውጤት ከ50% በታች ሆኖ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ውጤቱን ለአበዳሪው ተቋም እና ለቢሮው በቅጅ የማሳወቅ ስራ ይሰራል፤

10/ በአካባቢው የሚገኙትን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአካል በመመልከት በየሩብ ዓመቱ የአፈፃፀም ለውጥ ፕሮፋይል ያዘጋጃል፤

11/ በኢንቨስትመንት ስም የተላለፈ ማንኛውንም መሬት እና ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የተለየን መሬት የመከታተል፤የመጠበቅ ሙሉ ሃላፊነት ይወጣል

12/ በቢሮው የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል።

22.የጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1/ በአካባቢው የሚገኙትን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአካል በመመልከት በየሩብ ዓመቱ የአፈፃፀም ለውጥ ፕሮፋይል ያዘጋጃል፤

2/ የምርት ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት የእያንዳንዱን ባለሃብት ዓመታዊ የልማት አፈፃፀም በመስክ በመገኘት ይሞላል፤ ከውሳኔ አስተያየት ጋር ለቦርዱ ያቀርባል፤ የቦርዱን የውሳኔ አስተያየት ለመምሪያው ይልካል፤

3/ ለኢንቨስትመንት በተሰጠው መሬት ላይ በአግባቡ ማልማት ካልቻሉ ለአንድ ጊዜ የፁሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ማልማት ካልቻሉ መሬቱን ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ የውሳኔ አስተያይቱን ለቦርዱ በማቅረብ ያስወስናል፤ውሳኔውን ለመምርያ ያሳውቃል፤

4/ ከቀረጥ ነፃ የገባው ሃብት በተገቢው መንገድ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ፣ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ ይሰራል፣ከታለመለት ዓላማ ውጭ ያላዋሉትን እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ አስተያየት ለመምሪያ ያቀርባል፤

5/ ከኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ከመሬት አስተዳድርና አጠቃቀም የሚነሱ ችግሮች ካሉ ከመሬት መምሪያ ጋር በመቀናጀት ችግሩን ለይቶ ይፈታል፤ ከአቅም በላይ ከሆነ ለመምሪያው በሪፖርት ያሳውቃል፤

6/ የልማት አፈፃፀም ውጤት መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ጉድለት ያለባቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እንዲስትካከሉ ይደግፋል፣የአፈፃፀም ለውጥ ያመጡትን መምሪያ ያሳውቃል፤

7/ የመጠቀም መብት በእዳ ዋስትና በተያዘ መሬት ላይ የባለሃብቱ ዓመታዊ የልማት አፈፃፀም ውጤት ከ50% በታች ሆኖ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ውጤቱን ለአበዳሪው ተቋም እና ለመምሪያው በቅጅ የማሳወቅ ስራ ይሰራል፤

8/ በወረዳ ፤ዞንና ከተማ አስተዳደደርና በቢሮ ደረጃ በኢንቨስትመንት ስም የተላለፈ ማንኛውንም መሬት እና ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የተለየን መሬት የመከታተል፤ የመጠበቅ ሙሉ ሃላፊነት አለው፤

9/ ከቦርዱ መምሪያ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን የሚፈፅም ይሆናል።

23. ቴክኒክ ኮሚቴ ስለማቋቋም፡-

1/ የፕሮጀክት አፈፃፀም ገምጋሚ ቴክኒክ ኮሚቴ በዚህ መመርያ ተቋቁሟል፤

2/ የኮሚቴው ተጠሪነቱ በየደረጃው ለሚገኘው ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ኃላፊ ይሆናል፤

3/ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መዋቅር የሌላቸው ወረዳ ከተሞች ካሉ የልማት አፈፃፀም ውጤት በመምሪያው በኩል የሚሞላ ይሆናል።

24. የቢሮው የልማት አፈፃፀም ገምጋሚ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት፦

1/ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ድጋፍ እና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ---ሰብሳቢ፤

2/ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል 4 ባለሙያዎች ---------- አባላትና ከእነርሱ መካከል የሚመረጥ አንዱ ፀሐፊ።

25. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

1/ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ኢንዱስትሪ ዞን ቡድን መሪ ---------- ሰብሳቢ፤

2/ የፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል ባለሙያዎች 4 አባላት ----------አባል እና ከእነርሱ መካከል የሚመረጥ አንዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሠራል።

26. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ጽሕፈት ቤት ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

1/ የኢንቨስትመንት ማስፋፍያና ኢንዱስትሪ ዞን ቡድን መሪ ---------- ሰብሳቢ

2/ የፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል 4 ባለሙያዎች ---------- አባላት እና ከእነርሱ መካከል ተመርጦ አንዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሠራል።

3/ የፕሮጀክት ቴክኒክ ኮሚቴ ገምጋሚ ቁጥር አንድ ብቻ ከሆነ፤ ከተቋሙ ወስጥ ተቀራራቢ ሙያ ያለውን መርጦ ማሳተፍ ይቻላል።

27. ስለ እኩል ድምጽ

በውጤት አሰጣጡ ላይ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው ያለበት ተፈፃሚ ይሆናል።

28. የቢሮው ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1/ በቢሮው በኩል ልዩ ክልላዊ ፋይዳ ያላቸውን ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የልማት አፈፃፀም ለመገምገም ወደ መስክ ከመወጣቱ በፊት ቢያንስ ከ15 ቀናት ቀድሞ በየደረጃው በሚገኘው የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም በኩል መርሃ-ግብሩን እንዲያውቁት በኃላፊው አማካኝነት በደብዳቤ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፤

2/ መርሃ ግብሩ ተገልፆለት ሳይገኝ ከቀረ ኮሚቴው የራሱን አማራጭ ተጠቅሞ አፈፃፀሙን ከመምሪያዎች ወይም ከጽህፈት ቤቶች ጋር በመቀናጀት ልማት አፈፃፀም ውጤት ሊሞላ ይችላል፤ የአፈፃፀም ችግር ያለባቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ደግፎ ወደ ስራ ያስገባል፤

3/ የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም በተመለከተ ግዥ የተፈጸመበት ከሆነ ግዥ የተፈጸመበትን በምርት ዘመኑ ህጋዊ ደረሰኝ በማስቀረብ ማረጋገጥ፤ እንዲሁም ቴክኖሎጅና ማሽነሪ አቅርቦትና አጠቃቀም በተመለከተ በአካል በማየት የገዛ ስለመሆኑ ህጋዊ ደረሰኝ ከሚመለከታቸው የመንግስት ወይም ከግል ተቋማት እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ኪራይ የተጠቀመ ከሆነ የዘመኑን የኪራይ ውል ስምምነት ሊያቀርብ ይገባል፤

4/ በተዘጋጀው ቅፅ ላይ የልማት አፈጻጸም ውጤት በመስክ ተገኝቶ ይሞላል፤በቃለ-ጉባዔ እንዲደገፍ ያደርጋል፤ ስለመረጃው ትክክለኛነትን ባለሃብቶች ወይም ድርጅቶች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ ያደርጋል፤

5/ በአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ የግንባታ ውል፣ ዲዛይን እና የግንባታ ፈቃድ የመሳሰሉ መረጃዎችን በመያዝ የልማት አፈፃፀም ይገመግማል፣ ነጥብ ይሰጣል፣ በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለቢሮው ኃላፊ ያቀርባል፤

6/ ዓመታዊ የልማት አፈፃፀም ግምገማ ውጤት የተሞላላቸውን ፕሮጀክቶች መረጃ ይቀበላል፣ አደራጅቶ ይይዛል፤

7/ ዓመታዊ የልማት አፈፃፀም ግምገማ ውጤት የተሞላላቸውን ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከመምሪያዎች እና ጽህፈት ቤቶች ኢንቨስትመንት ቦርድ ተወስኖ ሲደርሰው መረጃውን አደራጅቶ ለቢሮ ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤የቢሮ ኃላፊ ውሳኔ ይሰጣል፤እንዳስፈላጊነቱ የክልሉንኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች ካሉ ከውሳኔ አስተያየትጋር በማቅረብ ያስወስናል፤

8/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው ይገመግማል፣ ከተፈቀደው ዓላማ ውጭ ያዋሉትን የውሳኔ አስተያየት በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለኃላፊ ያቀርባል፤ኃላፊው የውሳኔ አስተያየቱን ለሚመለከተው ተቋም ያሳውቃል፤

10/ ከቢሮው የሚሰጠውን ተጨማሪ ተግባርና አቅጣጫ ይፈፅማል።

29. <u>የመምሪያ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የልማት አፈፃፀም ለመገምገም ወደ መስክ ከመወጣቱ በፊት ቢያንስ ከ15 ቀናት ቀድሞ በየደረጃው በሚገኘው የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት

በኩል መርሃ ግብሩን እንዲያውቁት በኃላፊው አማካኝነት በደብዳቤ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፤

2/ መርሃ ግብሩ ተገልፆለት ሳይገኝ ከቀረ ኮሚቴው የራሱን አማራጭ ተጠቅሞ አፈፃፀሙን ከወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳድሮች ጋር በመቀናጀት ልማት አፈፃፀም ውጤት ሊሞላ ይችላል ፤ ሆኖም ግን የሜትሮ ፖሊታንና ሪጂኦ ፖሊታን ከተሞች የልማት አፈፃፀም ውጤት ይሞላሉ፤የአፈፃፀም ችግር ያለባቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ደግፎ ወደ ስራ ያስገባሉ፤

3/ በአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ ባለሀብቶች ወይም ድርጅቶች የግንባታ ውል፣ ዲዛይን እና የግንባታ ፈቃድ የመሳሰሉ መረጃዎችን በመያዝ የልማት አፈፃፀም ይገመግማል፣ ነጥብ ይሰጣል፤

4/ የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የግባአት አቅርቦትና አጠቃቀም በተመለከተግኝ የተፈጸመበትን ምርት ዘመኑ ህጋዊ ደረሰኝ በማስቀረብ ማረጋገጥ፤ እንዲሁም ቴክኖሎጅና ማሽነሪ አቅርቦትና አጠቃቀም በተመለከተ በአካል በማየት የገዛ ስለመሆኑ ህጋዊ ደረሰኝ ከሚመለከታቸው የመንግስት ወይም ከግል ተቋማት እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ኪራይ ተጠቀመ ከሆነ የዘመኑን የኪራይ ውል ስምምነት ሊያቀርብ ይገባል፤

5/ የእያንዳንዱን ፕሮጀክት የልማት አፈፃፀም በተዘጋጀው ቅፅ ላይ የልማት አፈፃፀመው ውጤት ይሞላል፤ በቃለ-ጉባዔ እንዲደገፍ ያደርጋል፤ስለመረጃው ትክክለኛነት ባለሀብቱ፣ድርጅቱ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ ያደርጋል፤

6/ በየደረጃው በሚገኝ ወረዳና ከተማ አስተዳድር ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት የውሳኔ አስተያየት ተሰጥቶ የተላኩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የልማት አፈፃፀም መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፣ለቢሮው ያሳውቃል፤

7/ በየደረጃው በሚገኝ ኢንቨስትመንት ቦርድ የውሳኔ አስተያየት የተሰጠባቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከውሳኔ አስተያየት ጋር በትይዩ ላለ ቦርድ ያቀርባል፣የቦርዱን የውሳኔ አስተያየቱን ለቢሮው አደራጅቶ ይልካል፤

8/ በኢንቨስትመንት ስም የተላለፈን መሬት እና ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የተዘጋጀ መሬት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ መዝግቦ ይይዛል፤

9/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው ያረጋግጣል፣በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለመምሪያ ኃላፊ ያቀርባል፤

10/ በልማት አፈጻጸም ነጥብና ውሳኔ አሰጣጥ ወቅት የኮሚቴ አባላት እኩል ድምጽ ይኖራቸዋል፤ሆኖም የከሚቴ አባላት እኩል ድምጽ ከመጣ ሰብሳቢው የሚደግፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል።

11/ በክልሉ የኢንቨስትመንት ቦርድ እና በቢሮው የሚሰጡ ውሳኔዎችን እና አቅጣጫዎችን ይፈፅማል፤ይከታተላል፤

30. <u>ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ጽሕፈት ቤት ቴክኒክ ኮሚቴ</u>

1/ የልማት አፈፃፀም ለመገምገም ወደ መስክ ከመወጣቱ በፊት ቢያንስ ከ 15 ቀናት ቀድሞ መርሃ ግብሩን ለባለሃብቶች፣ለድርጅቶች ወይም ለህጋዊ ወኪሎቻቸው በጽ/ቤቱ ኃላፊ አማካኝነት በደብዳቤ እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

2/ መርሃ ግብሩ ተገልፆለት ሳይገኝ ከቀረ ኮሚቴው የራሱን አማራጭ ተጠቅሞ አፈፃፀሙን መርሃ ግብሩን ሳያሳውቅ ቢቀር ተጠያቂ ይሆናል፤

3/ በአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ ባለሀብቶች ወይም ድርጅቶች የግንባታ ውል፣ ዲዛይን እና የግንባታ ፈቃድ የመሳሰሉ መረጃዎችን በመያዝ የልማት አፈፃፀም ይገመግማል፣

4/ ተገምግመው ውሳኔ ያገኙና ውል የተሰጣቸው የግብርና፤ ሆርቲካልቸርና አገልግሎት ፕሮጀክቶች በተመለከተ በመስክ የተገኘውንና ከሌሎች የመረጃ ምንጭ ያገኘነውን መረጃ መሰረት በማድረግ ነጥብ ይሰጣል፤ ውጤት ይሞላል፤ በቃለ-ጉባዔ እንዲደገፍ ያደርጋል፤ ስለመረጃው ትክክለኛነት ባለሀብቱ፣ ድርጅቱ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ ያደርጋል፤

5/ የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የግባአት አቅርቦትና አጠቃቀም በተመለከተ ግዥ የተፈጸመበት ከሆነ ግዥ የተፈጸመበትን ምርት ዘመኑ ህጋዊ ደረሰኝ በማስቀረብ ማረጋገጥ፤ እንዲሁም ቴክኖሎጅና ማሽነሪ አቅርቦትና አጠቃቀም በተመለከተ በአካል በማየት የገዛ ስለመሆኑ ህጋዊ ደረሰኝ ከሚመለከታቸው የመንግስት ወይም ከግል ተቋማት እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ኪራይ ተጠቀመ ከሆነ የዘመኑን የኪራይ ውል ስምምነት ሊያቀርብ ይገባል።

6/ የልማት አፈፃፀም የተሞላላቸውን ፕሮጀክቶች ቃለ ጉባኤ እና የእያንዳንዱን ባለሃብት ወይም ድርጅት ፕሮፋይል ከውሳኔ አስተያየት ጋር ለማኔጅመንቱ ያቀርባል፣ ኃላፊውም የማኔጅመንቱን የውሳኔ አስተያየት ለቦርዱ በማቅረብ የቦርዱን የውሳኔ አስተያየት ለመምሪያው ያሳውቃል፤

7/ የተለያዩ የጉምሩክ ቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆኑ ባለሃብቶች ወይም ድጅቶች ለታለመለት ዓላማ ማዋላቸውን ይከታተላል፤ በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የውሳኔ አስተያየት ለሃላፊው ያቀርባል፣ኃላፊውም የወሳኔ አስተያየቱን ለመምሪያው ያሳውቃል፤

8/ በኢንቨስትመንት ስም የተላለፈን መሬት እና ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የተዘጋጀ መሬት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ መዝግቦ ይይዛል፤

9/ በአካባቢው በተለያየ ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩ እና የተለያዩ የጉምሩክ ቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆኑ ባለሃብቶችንወይምድጅቶችን የልማት አፈፃፀም ይገመግማል፣ነጥብ ይሰጣል፣ በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለሃላፊው ያቀርባል፣

10/ በቢሮው እና መምሪያው የሚሰጡ ውሳኔዎችን እና አቅጣጫዎችን ይፈፅማል፣ይከታተላል፤

31. <u>የኢንቨስትመንት መሬት ኪራይ ውል እድሳት ወይም ማሻሻያ የሚከናወነው</u>

1/ የውል ጊዜው ከመጠናቀቁ ከአምስት ወር በፊት ጥያቄውን ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም በጽሑፍ ሲያሳውቅ፤

2/ በተለያዩ ምክንያቶች የመሬት መጠን ለውጥ ሲያጋጥም፤

3/ የመሬት ሁኔታ ለተፈቀደለት ፕሮጀክት ተስማሚነት ከሌለው በየደረጃው በሚገኙ የመሬት ተቋም ከመሬት አጠቃቀም ህጉ ጋር የማይጋጭ ሆኖ ሲገኝ፤

4/ ስልጣን ባለው አካል የፀደቀ የንግድ ስም እና የመመስረቻ ጽሑፍ ሲያቀርብ፤

5/ በተከታታይ አመታት ከፍተኛ የልማት አፈፃፀም የአፈጻጸም ውጤት እያስመዘገበ ከመጣ በወጣው ወቅታዊ የመሬት ሊዝ ዘመን መሰረት

6/ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት ብድር ለመክፈል ያልቻለ ባለሃብት ተጨማሪ ብድር ጥያቄ አቅርቦ በአበዳሪ ተቋሙ ተቀባይነት ካገኘ እና ማስረጃ ካቀረበ ውል እንዲራዘምለት ከጠየቀበት ቀን ጀምሮ በሚመለከተው ተቋም በወጣው ወቅታዊ ሊዝ ዘመን መሰረት እንዲራዘምለት ይደረጋል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከገንዘብ አበዳሪ ተቋማት አዲስ ብድር ለማግኘት አስፈላጊውን መመዘኛ አሟልተው ቀሪ የውል ዘመናቸው አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት መበደር ያልቻሉ ባለሀብቶች ወይም ድርጅቶች ጥያቄ ከቀረበበት ጊዜ ቅርብ የሆነው ውጤት አጥጋቢ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ወቅታዊ ሊዝ ዘመን መሰረት እንዲራዘምለት ይደረጋል፤

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) የተመለከተው እንዳለ ሆኖ ቅርብ የሆነውን የልማት አፈፃፀም ግምገማ ውጤት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ውጤቱ ካልተሞላ ወይም

ውጤቱ ከአጥጋቢ በታች ቢሆንም ችግሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ እና ቢሮው ካመነበት ውሉ ሊራዘም ይችላል።

32. የፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደት በተመለከተ

1/ ለአነስተኛ እና ለመካከለኛ ግንባታ የሊዝ ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም ለከፍተኛ ግንባታ ከሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በሚመለከተው ተቋም የግንባታ ፈቃድ ያወጣል፤ ሆኖም በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለሃብቱ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ዲዛይኑን ካላቀረበ ግንባታ የሚጀምርበት ጊዜ ስሌት የሚጀምረው የሊዝ ውል ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

2/ ለአገልግሎት ዘርፉ የግንባታ ፈቃድ ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ የግንባታ መጀመሪያ የጊዜ ስሌት ሆኖ በሚመለከተው ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ባወጣው አሰራር መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።

3/ በሊዝ ሥርዓት እንዲያለማ የተፈቀደለት ባለሀብት ወይም ድርጅት የግንባታ ፈቃድ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ለግንባታ ደረጃው በተቀመጠው የግንባታ መጀመሪያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ መጀመር አለበት፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገዉ ቢኖርም ለግንባታ መጀመሪያ በተቀመጠዉ ጊዜ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክኒያት ግንባታ ያልተጀመረ መሆኑን ተጨባጭ ማስረጃ በባለጉዳዩ ከቀረበ ቢሮው ጉዳዩን መርምሮ የግንባታ ማራዘሚያ ጊዜ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ከአቅም በላይ ተብለው የሚወሰደ ችግሮች፡-

ሀ) ቦታው ላይ የይገባኛል ክርክር ኖሮበት የፍርድ ቤት እግዳ ካለ፤

ለ) ከሶስተኛ ወገን ያልጸዳ ወይም ቦታውን ነፃ አድርጎ ማስረከብ ካልተቻለ፤

ሐ) የሊዝ ወይም ኪራይ ዉል ተቀባይ የጤና ችግር ሲያጋጥመው እና ይህም ዕውቅና ካለው የጤና ተቋም በሐኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

መ) የሊዝ ወይም ኪራይ ውል ተቀባይ በህግ ጥላ ስር ሲውል፤

ሠ) የሊዝ ወይም ኪራይ ዉል ተቀባይ በሞት ሲለይና ወራሾች የማሳወጅ ሂደት ጊዜ ሲወስድባቸው፤

ረ) ሌሎች ከአቅም በላይ ተብለው በሕግ እውቅና ያላቸውን ምክንያቶች ያካትታል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም በሚመለከተው ተቋም የሚሰጠው የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ ማራዘሚያ ከማስጠንቀቂያ ጋር ኮንስትራክሽን ባለስልጣኑ አሰራር መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።

7/ እንደየ ፕሮጀክቱ ባህሪ የሚለያይ ሆኖ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል፤

8/ ለእርሻ ኢንቨስትመንት ዝቅተኛ የግንባታ ደረጃ ግድግዳው በእንጨት ሆኖ ጣራው በቆርቆሮ መሰራት ይኖርበታል፤

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የብሎኬት እና መሰል ግንባታ G+0 ሊገነባ ይችላል፤

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት ውል የሰጠው አካል ሲፈቅድ G+1 እና በላይ ህንጻ ሊገነባ ይችላል፤

33. ለአገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለተፈራ ንብረት የስመ ንብረት ዝውውር

1/ የንግድ ፈቃድ ከማውጣቱ በፊት በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ለሌላ ባለሃብት ማስተላለፍ የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት ጥያቄውን ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም በማቅረብ የቀረበው ጥያቄ አግባብ ያለውና አሰራሩን የተከተለ ስለመሆኑ አረጋግጦ ለሚመለከተው ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጣል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮጀክቱን 50% ሲያጠናቅቅ በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ይችላል፤ ሆኖም ግን ባለሃብቱ ወይም ድርጅቱ ባቀረበው የአዋጭነት ጥናት ሰነድና በገባው ውል መሰረት ማልማት ካልቻለ በባለሙያ ግምት መሰረት ከመሬት በላይ ላለማው የንብረት ካሳ አዲስ የሚገባው ባለሃብት ወይም ድርጅት ወይም ወረዳው ከተማው ግምቱን ይከፍላል፤

3/ የስመ-ንብረት ዝውውር የሚፈፀመው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ማስረጃዎች ሲሟላ ይሆናል፤

ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፤

ለ) የፀደቀ የግንባታ ፕላን ከሥራ ዝርዝር ግምት (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ) ጋር ሲቀርብ፤

ሐ) በፀደቀው ፕላን መሰረት ስለመሰራቱ እና ግንባታው ያለበት ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ ሲቀርብ፤

መ) ውዝፍ እዳ ስላለመኖሩ ማስረጃ ሲኖር፣ የሊዝ ክፍያ ካለበትም የገዛው ግለሰብ ወይም ድርጅት ቀሪ ክፍያውን ለመክፈል ስምምነቱን የሚገልፅ ማስረጃ ሲቀርብ፤

ሠ) ከባንክ እና ከፍርድ ቤት እግድ ስላለመኖሩ ማስረጃ ሲቀርብ፤

ረ) በዉርስ የሚዞር ከሆነ የዉርስ ባለመብትነትን የሚያረጋግጥ የፍርድቤት ዉሳኔ ማስረጃ ሲቀርብ፤

ሰ) በግዥና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት በውክልና ከሆነ ሕጋዊ ውክልና ሲቀርብ፤

ሸ) በግዥና ሻጭ መካከል የውል ስምምነት በአካል ቀርበው በባለሙያ ፊት የተፈራረሙበትንና የእማኞች ፊርማ ያለበት ማስረጃ ሲያቀርብ፤

ቀ) ይገባኛል የሚል አካል ስላለመኖሩ የሚገልፅና 15 ቀን በአየር ላይ የቆየ ማስታወቂያ ሲቀርብ ይሆናል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

34. የባለሀብት ወይም የድርጅቶች መብትና ግዴታዎች፤

1/ የባለሃብቱ ወይም ድርጅቱ መብት

ሀ) አንድ ባለሀብት ወይም ድርጅት መሬት ተረክቦ ለማልማት ፕሮጀክት እና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶችን በማቅረብ ተወዳድሮ ካለፈ መሬት ማግኘት እና ማልማት ይችላል፤

ለ) የተሰጠውን የፕሮጀክት ልማት አፈፃፀም ውጤት ግልፅ ካልሆነለት ቴክኒክ ኮሚቴውን ጠይቆ መረዳት ይችላል፤

ሐ) ባለሀብቱ ወይም ድርጅቱ ከቴክኒክ ኮሚቴው የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ካሉ ማግኘት ይችላል፤

መ) ባለሀብቱ ወይም ድርጅቱ የኢንቨስትመንት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት የማበረታቻ ተጠቃሚ የመሆን

2/ የባለሃብቱ ወይም ድርጅቱ ግዴታዎች

ሀ) በተሰጠውን መሬት ላይ ስላለማው ልማት አፈፃፀም ለቴክኒክ ኮሚቴው ፕሮጀክቱን በመስክ የማሳየት እና ለሚጠየቀው ጥያቄ በቃል ፣ በፅሑፍም ሆነ በቪዲዮ ወይም ፎቶግራፍ ሙሉ መረጃ መስጠት አለበት፤

ለ) የመሬት ውል ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ የፕሮጀክት አፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ፕሮጀክቱ ባለበት ጽህፈት ቤትበተዘጋጀው የሪፖርት ቅፅ መሠረት መላክ አለበት።

35. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ሰርኩላር ወይም ልማዳዊ አሠራር ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ አይሆንም።

36. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት .....ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ መመርያው ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ያለ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ዉጤት የሚኖረው መመርያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአብክመ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ድረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ

እንድሪስ አብዱ አህመድ

ቢሮ ሃላፊ